# 2009 H1N1 የእንፍሉዌንዛ ክትባት

***ላይቭ፣ አቴኔትድ (LIVE, ATTENUATED)***
***(በአፍንጫ ውስጥ በመርጨት የሚሰጥ ክትባት)***

**ማወቅ ያለብዎት ነገር**

ስለ ክትባት ብዙ መረጃዎች በስፓኒሽ እና ሌሎች ቋንቋዎች ተተርጉመው ይገኛሉ። በዚህ ድረገጽ ይመለከቱ፣ www.immunize.org/vis.

## 1 የ2009 H1N1 እንፍሉዌንዛ ምንድነው?

የ2009 H1N1 እንፍሉዌንዛ (አንዳንድ ጊዜ ስዋይን ፍሉ ተብሎ የሚጠራ) አዲስ በሆነው የእንፍሉዌንዛ ዝርያ የሚከሰት ነው። ወደ ብዙ አገሮች ደግሞ ተዳርሰዋል።

ልክ እንደ ሌሎች የፍሉ ቫይረሶች፣ የ2009 H1N1 ከሰው ወደ ሰው በመሳል፣ በማስነጠስ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በቫይረሱ የተበከሉ ነገሮችን በመያዝ ይተላለፋል።

የ2009 H1N1 ምልክቶች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያካትታል፥
• ድካም • ትኩሳት • የጉሮሮ መቁሰል • የሰውነት መቆረጣጠም
• ብርድ ብርድ ማለት • ሳል • ማስነጠስ

እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች የተቅማጥ እና የማስመለስ ምልክቶች ይታይባቸዋል።

ብዙ ሰዎች ከታመሙ በኃላ በአንድ ሳምንት ውስጥ ይሻላቸዋል። ነገር ግን በአንዳንድ ሰዎች ላይ ኑሞንያ ወይም ሌላ ካባድ በሽታ ሊያስከትል ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ሆስፒታል ሊገቡ ኣንድዳንድ ደግሞ ሊሞቱ ይችላሉ።

## 2 የ2009 H1N1 ከሌሎች የተለመዱ (በየወቅቱ የሚከሰቱ) ፍሉ እንዴት ሊለይ ይችላል?

በየወቅቱ የሚከሰቱ የፍሉ ቫይረሶች ከአመት ወደ አመት የሚለያዩ ሲሆኑ እርስ በርሳቸው ግን ብዙ መተሳሰር አላቸው።

ከአሁን በፊት በፍሉ በሽታ የተለከፉ ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ ሰውነታቸው ለወቅቱ ፍሉ ቫይረስ የመቋቋም ችሎታ ይኖረዋል (ሰውነታቸው ቫይረሱን የመዋጋት ችሎታን ያዳብራል)።

የ2009 H1N1 የፍሉ ቫይረስ፣ አዲስ የቫይረስ ዝርያ ነው። ከወቅቱ የፍሉ ቫይረስ በጣም የተለየ ነው።

ብዙ ሰዎች ለ2009 H1N1 ፍሉ፣ ዝቅተኛ የመቋቋም ችሎታ ወይም ደግሞ ምንም የመቋቋም ችሎታ የላቸውም (ሰውነታቸው ቫይረሱን ለመዋጋት ዝግጁ አይደለም)።

## 3 የ2009 H1N1 እንፍሉዌንዛ ክትባት

የ2009 H1N1 እንፍሉዌንዛ የሚከላከል ክትባቶች አሉ፥

- እነዚህ ክትባቶች ልክ እንደ የወቅቱ ፍሉ ክትባት ነው የተሰሩት።
- ደህንነታቸው እና ውጤማነታቸው ልክ እንደ የወቅቱ ፍሉ እንዲሆኑ ይጠበቃሉ።
- በሌሎች ቫይረሶች ለሚከሰቱ "እንፍሉዌንዛን የሚመስሉ" በሽታዎች መከላከል አይችሉም።
- በወቅቱ ከሚከሰቱ የፍሉ ዓይነቶች ሊከላከሉ አይችሉም። ***በወቅቱ የሚከሰት ፍሉን ለመከላከል ከፈለጉ፣ የወቅቱ እንፍሉዌንዛ ክትባት መውሰድ አለብዎት።***

**ላይቭ አቴናተድ ኢንትራናዛል (Live, attenuated intranasal)** ወይም LAIV የተባለውን ክትባት፣ በአፍንጫ እንዲወሰድ ይደረጋል። **ይህ ጽሁፍ ስለ ላይቭ አቴናትድ ኢንትራናዛል ክትባት ያወራል።**

በመርፌ በመወጋት የሚሰጥ፣ ኢንአክቲቬትድ (inactivated) የተባለውን ክትባት ደግሞ አለ። በሌላ ጽሑፍ ተገልጸዋል።

የ2009 H1N1 LAIV ቲመሮሳል **(thimerosal)** ወይም ሌላ ዓይነት ፕረሰርቫቲቭስ (preservatives) የለውም። ከ2 እስከ 49 የዕድሜ ክልል ያሉት ሰዎች እንዲወሰዱት ይፈቀዳል።

የክትባቱ ቫይረስ ስለተዳከመ በሽታ አያስከትልም።

## 4 የ2009 H1N1 የእንፍሉዌንዛ ክትባት ማን መውሰድ አለበት፤ መቼ መወሰድ አለበት?

**ማን**

LAIV ከ2 እስከ 49 የዕድመ ክልል ያሉት፤ እርጉዝ ያልሆኑና እንዲሁም ሌላ ዓይነት የጤንነት ችግር የሌላቸው ሰዎች ቢወስድ ጉዳት እንደሌለው ተረጋግጠዋል (እታች ቁጥር 5 ይመለከቱ)። የ2009 H1N1 LAIV መውሰድ የሚችሉ ሰዎች በመጀመርያ ደረጃ ጤነኞች ሲሆኑ፤ እንዲሁም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች የሚመለከታቸው ናቸው፥

- እድሜያቸው ከ2 እስከ 24 ዓመት የሆኑ፣
- እድሜያቸው ከ25 እስከ 49 ዓመት የሆኑ እንዲሁም
  - ከ6 ወር በታች እድሜ ያላቸው ህጻናት ጋር የሚኖሩ ወይም የሚንከባከቡ፣ ወይም ደግሞ
  - በጤና እንክብካቤ ወይም ኢመርጀንሲ ክፍል የሚሰሩ

እንዲሁም ተጨማሪ ክትባቶች ሲመጡ፣ ሌሎች ጤንነታቸው የተሟላ ከ25 እስከ 49 የእድሜ ክልል ያሉት ሰዎችም መከተብ አለባቸው።

> ማሳሰብያ፣ አንዳንድ ሰዎች LAIV መውሰድ የለባቸውም - ለምሳሌ እርጉዝ ሴቶች፣ ለረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያላቸው ሰዎች፣ እንዲሁም ከ 6 ወር እስከ 2 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉት ህጻናቶች - ነገር ግን መከተባቸው በጣም አስፈላጊ ነው። የፍሉ ክትባትን መውሰድ አለባቸው።

የፌደራላዊ መንግስት ይህንን ክትባት ወደው መውሰድ ለሚፈልጉ ሰዎች ብቻ ይሰጣል። ነገር ግን የስቴት ሕግ ለአንዳንድ ሰዎች ክትባቱን እንዲወሰዱ ሊያስገድድ ይችላል።

**መቼ**

ክትባቱ ሲመጣ በተቻለ መጠን ቶሎ ብለው ይከተቡ።

እስከ 9 ዓመት ዕድሜ ያሉት ልጆች ሁለት የክትባት መጠን መውሰድ አለባቸው፡ ይህም በመካከሉ የአንድ ወር ጊዜ መኖር አለበት። እድሜያቸው ከዛ በላይ የሆኑ ልጆች እና አዋቂዎች የአንድ ጊዜ መጠን ይወስዳሉ።

## 5 አንዳንድ ሰዎች ክትባቱ መውሰድ የለባቸውም ወይም ደግሞ መጠበቅ ይኖርባቸዋል

**የእንቁላል ወይም ሌላ በክትባቱ ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር ከባድ (ለህይወት አስጊ የሆነ) አለርጂ ካልዎት** የ2009 H1N1 LAIV መውሰድ የለብዎትም። *ማንኛውም ዓይነት ከባድ አለርጂ ካልዎት፡ ክትባቱ ለሚሰጠው ሰው ማሳወቅ አለብዎት።*

የ2009 H1N1 LAIV ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሰዎች መስጠት አይገባም፥

- ከ2 ዓመት በታች ዕድሜ ላላቸው ልጆች እና ከ50 ዓመት በላይ ለሆኑ አዋቂዎች
- እርጉዝ ሴቶች፣
- በሽታን የመከላከል ዓቅሙ ደካማ ለሆነ ሰው፣
- ለረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያለው ሰው፡ ለምሳሌ
  - የልብ ድካም - የኩላሊት ወይም የጉበት በሽታ
  - የሳንባ በሽታ - የሞታቦሊክ በሽታ እንደ የስኳር በሽታ የመሳሰሉት
  - የአስም በሽታ - አነሚያ እና ሌሎች የደም በሽታዎች
- የአስም በሽታ ያላቸው ከ5 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ልጆች ወይም ደግሞ ባለፈው ዓመት አንድ ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ የማስተንፈስ ችግር ያሳዩ፣
- የመስተንፈስ ወይም የመዋጥ ችግር ሊይስከትል የሚችል የሰውነት መቆረጣጠም ወይም የነርቭ በሽታ (እንደ ሰረብራል ፓልሰይ የመሳሰሉት) ያላቸው ሰዎች፣
- በአያሌው ዝቅተኛ የሆነ በሽታን የመከላከል አቅም ካለው ሰው (በልዩ እና የተከለለ ቦታ እንክብካቤ ለሚያስፈልገው፡ ለምሳሌ በቦን ማረው ትራንስፐላንት ክፍል ቦታ የሚገኝ) ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው፣
- ለረጅም ጊዜ የአስፐሪን መድሀኒት የሚወስዱ ልጆች ወይም አዋቂዎች

ትንሽ፡ ወይም ደግሞ በጠና የታመሙ፡ ክትባቱ ከመውሰድዎ በፊት ከህመምዎ እስከሚድኑ ድረስ መጠበቅ ይኖርብዎታል። ቀላል የሆነ ጉንፋን ወይም ሌላ በሽታ ከታመሙ፡ የግድ መጠበቅ የለብዎትም።

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች የሚመለከትዎ ከሆነ ሐኪምዎን ያሳውቁ፥

- አንድ የወቅቱ ፍሉ የክትባት መጠን ከወሰዱ በኃላ ለህይወትዎ የሚያሰጋ አለርጂ አይተው የሚያውቁ ከሆነ፣
- የGuillain-Barre ሰይንድሮም (GBS ተብሎም የሚጠራ ሀይለኛ የሽባነት በሽታ)።

እነዚህ ክትባቱን እንዳይወስዱ የሚከለክሉ ምክንያቶች ላይሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን የህክምና ሰራተኞቹ ምን ዓይነት ውሳኔ መወሰን እንደሚችሉ ምክር ሊሰጥዎት

የ2009 H1N1 LAIV ከሌሎች የክትባት አይነቶች ጋር በአንድ ላይ ሊሰጥ ይችላል። ባለፈው ወር ማንኛውም ዓይነት ክትባት ወስደው ከሆነ ወይም ደግሞ ለሚመጣው ወር ለመውሰድ እቅድ ካልዎት፡ ሐኪምዎን ያሳውቁ። የ2009 H1N1 LAIV እንዲሁም የወቅቱ የLAIV ክትባት በአንድ ላይ መወሰድ የለባቸውም።

## 6 የ2009 H1N1 LAIV የሚያስከትለው አደጋ ምንድነው?

ክትባት፡ ልክ እንደ ማንኛውም ዓይነት መድሀኒት ከባድ ችግር ሊያስከትል ይችላል፤ ለምሳሌ፡ ከባድ የአለርጂ በሽታ። ነገር ግን ማንኛውም ዓይነት ክትባት፡ ከባድ ጉዳት፡ ወይም ሞት የማስከተል ዕድል እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው።

የ2009 H1N1 LAIV ሊያስከትለው የሚችል ጉዳት የወቅቱ LAIV ሊይስከትለው ከሚችለው ጉዳት ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ይጠበቃል።

**ቀላል የሆኑ ችግሮች፥**

አንዳንድ ከ 2 እስከ 17 የእድሜ ክልል ያሉት ልጆች እና ወጣቶች የሚከተሉትን ቀላል የሆኑ ችግሮች እንዳጋጠማቸው ይዘግባሉ፥

- ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ፣ የአፍንጫ መደፈን እና ሳል
- ትኩሳት
- የራስ ምታት እና የጡንቻዎች መቆረጣጠም
- የመተንፈስ ችግር
- የሆድ መቆረጥ ወይም አልፎ አልፎ የማስመለስ ወይም የተቅማጥ ምልክቶች

አንዳንድ ከ18-49 የእድሜ ክልል ያሉ አዋቂዎች የሚከተሉትን ይዘግባሉ፥

- ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ ወይም የአፍንጫ መደፈን
- የጉሮሮ መቁሰል
- ሳል፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ድካም/ሀይል ማጣት
- የራስ ምታት

**ከባድ የሆኑ ችግሮች**

- በክትባቱ የሚከሰቱ ለህይወት የሚያሰጉ አለርጂዎች ቁጥራቸው በጣም አንስተኛ ነው። ካጋጠሙ ብዙ ጊዜ ክትባቱ ከተወሰደ በኃላ ከጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰዓቶች ይሆናል።
- በ1976 ዓ.ም፡ የበፊቱ የ ኢንአክቲቨተድ ሰዋይን ፍሉ ክትባት የ Guillain-Barre ሰንድሮም (GBS) አስከትሎ ነበር። LAIV ግን ከGBS ጋር መተሳሰር የለውም።

## 7 ከባድ የሆነ ችግር ካስከተለስ?

**ምን ዓይነት ነገር ማስተዋል አለብኝ?**

ማንኛውም ያልተለመደ ነገር፡ ለምሳሌ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም የጠባይ መለዋወጥ። ከባድ የሆነ የአለርጂ በሽታ ምልክቶች እንደ የእስትንፋስ ማጠር፣ የጉሮሮ ድምጽ ማሰማት፣ የቆዳ ማሳከክ፣ መቅላት ወይም ማበጥ፣ ድካም፣ የልብ ምታት መፍጠን፣ ወይም ደግሞ ጭው ማለት ያጠቃልላል።

**ምን ማድረግ ይኖርብኛል?**

- ወደ ሀኪምዎ **ይደውሉ፤** ወይም ደግሞ የታመመውን ሰው ቶሎ ብለው ወደ ሐኪም ቤት ይውሰዱት።
- ያጋጠመውን ነገር ሐኪሙን **ይንገሩ።** ያጋጠመውን ቀን እና ጊዜ እንዲሁም ክትባቱ የተወሰደበት ቀን።
- አገልግሎት ሰጪውን በሽታውን በተመለከተ የAdverse Event Reporting System (VAERS) ቅጽ እንዲሞላ **ጠይቁት።** ወይም ደግሞ እርስዎ በVAERS ድረገጽ **www.vaers.hhs.gov** ወይም ደግሞ ወደ **1-800-822-7967** በመደወል ሪፖርቱን ሞምላት ይችላሉ።

*VAERS የሕክምና ምክርን አይሰጥም።*

## 8 የክትባት ጉዳት ካሳ

ክትባቱ በእርስዎ ወይም በልጅዎ ላይ ጉዳት ካደረሰ፡ ክስ እንዲያቀርቡ ያልዎት እድል በህግ በጣም የተወሰነ ነው።

ነገርግን፡ በክትባቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበትን ሰው ለማሳከም የህክምና አገልግሎት ወይም ሌሎች ወጪዎችን ለመክፈል የሚረዳዎ የፌደራል የሆነ ፕሮግራም ተቋቁመዋል። ይህ ፕሮግራም በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወደ **1-888-275-4772** ይደውሉ ወይም በ **www.hrsa.gov/countermeasurescomp/default.htm** ይመለከቱ።

## 9 ከዚህ የበለጠ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

- አገልግሎት ሰጪውን ያነጋግሩ። የክትባቱ መረጃ ፓኬጅ ሊሰጥዎት ወይም ደግሞ ስለሌላ የመረጃ ምንጭዎች ምክር ሊሰጥዎት ይችላሉ።
- ወደ በአከባቢዎ ወይም በሚኖሩበት ስቴት የሚገኘውን የጤና ጥበቃ ክፍል ይደውሉ፣
- የCenters for Disease Control and Prevention (CDC) ይጠይቁ
  - በስ.ቁ **1-800-232-4636 (1-800-CDC-INFO)** ይደውሉ፡ ወይም
  - የCDC ድረገጽን **www.cdc.gov/h1n1flu** ወይም **www.cdc.gov/flu** ይመለከቱ
  - በ **www.flu.gov** ይመለከቱ

DEPARTMENT OF HEALTH AND HUMAN SERVICES
CENTERS FOR DISEASE CONTROL AND PREVENTION

Vaccine Information Statement
2009 H1N1 LAIV - Amharic 10/2/09

Translation provided by the Minnesota Department of Health